# ለICE ድንገተኛ አሰሳ ይዘጋጁ

እርስዎ በሌሉበት ጊዜ ልጅዎን የሚንከባከብ እና ውሳኔዎችን የሚሰጥ ተጠባባቂ አሳዳጊ ይመድቡ። የጠበቃዎን ስልክ ቁጥር በቃልዎ ይያዙ እና በመመዝገብ ከእርስዎ በፍፁም እንዳይለይ። ዕቅድ ያውጡ እና ለሚያምኗቸው ጓደኞች ወይም ቤተሰብ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ይስጡ፦

- ★ የግል ዝርዝሮች (ስም፣ SSN/ITIN፣ የ"A-ቁጥር"፣ የትውልድ ቦታ)
- ★ የእውቂያ መረጃ (የአደጋ ጊዜ ተጠሪዎች፣ ጠበቃ፣ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ)
- ★ የቤተሰብ ዝርዝሮች (የልጆች ሞግዚቶች፣ ሐኪሞች፣ የመድኃኒት መረጃ፣ አለርጂዎች/የምግብ ፍላጎቶች)

# በICE እንዲቆሙ ከተደረጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

የአሜሪካ ዜጋ ካልሆኑ፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦

- ★ ዝም ይበሉ እና ይረጋጉ።
- ★ በሩን አይክፈቱ ወይም ወደ ውስጥ አያስገቧቸው።
- ★ የመያዣ/የእስር ማዘዣ እንዲያሳዩዎት ይጠይቁ።
- ★ ፍተሻ/ብርበራ ለማድረግ ሲጠየቁ አይሆንም (እምቢ) ይበሉ።
- ★ መታወቂያዎን፣ የስራ ፈቃድዎን ወይም ማናቸውንም ሰነዶች መስጠት የለብዎትም።
- ★ በፍጹም ሀሰተኛ ሰነዶችን አያሳዩ ወይም የአሜሪካ ዜጋ ነኝ ብለው አይዋሹ።

# በDMV (የኮሎምቢያ፣ ሜሪላንድ እና ቨርጂኒያ ዲስትሪክት) ውስጥ ከICE ጋር ሲገናኙ መብቶችዎን ይወቁ

የግዛት/ስቴት ድንበሮችን ሲያቋርጡ እነዚህ መብቶች አይለወጡም።

ACLU DC ACLU MD ACLU VA

# እርዳታ የት ማግኘት እንደሚችሉ

የኢሚግሬሽን ተሟጋቾች ኔትዎርክ www.immigrationadvocates.org

የአሜሪካ የኢሚግሬሽን ጠበቆች ማህበር www.ailalawyer.com

ነጻ የሕግ አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር፣ (የፍትህ መምሪያ)፦
www.justice.gov/eoir/file/probonofulllist/dl

የጥገኝነት ተሟጋችነት: https://asaptogether.org/es

የኦንላይን እስረኛ ማፈላለጊያ ሥርዓት
https://locator.ice.gov/odls/#/search

ሂዩማን ራይትስ ፈርስት: https://readynow.app.link/download

የስልክ መስመር 202-335-1183
https://www.dcmigrantmutualaid.org/hotline




# በICE ቁጥጥር ስር ከዋሉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

- ★ ዝም ይበሉ እና ይረጋጉ።
- ★ ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታዎ አይወያዩ ወይም በማንኛውም ነገር ላይ አይፈርሙ።
- ★ አስተርጓሚ እንደሚያስፈልግዎት ይናገሩ።
- ★ መክፈል ባይችሉም እንኳ ጠበቃ የማግኘት መብት አለዎት።
- ★ ስልክ የመደወል መብት አለዎት፣ ነገር ግን ከጠበቃዎ ጋር ካልሆነ በስተቀር ንግግሮቹ ክትትል ይደረግባቸዋል።




የICE የመያዣ ማዘዣ (ቅጽ 1-200) ICE ወደ ቤትዎ እንዲገባ ፈቃድ አይሰጠውም። በዳኛ የተፈረመ የወንጀል ማዘዣ ICE ወደ ቤትዎ እንዲገባ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

ስለሚከተሉት ጉዳዮች ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አይጠበቅብዎትም፦

- ★ ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታዎ።
- ★ የት እንደተወለዱ።
- ★ አገሪቱ ውስጥ እንዴት እንደገቡ።

ICE ወደ ቤትዎ ወይም የሥራ ቦታዎ ቢመጣ፣ እንዲሁም እያሽከረከሩ ሲያስቁምዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎት መረጃ ለማግኘት ወደ acluva.org/kyr-dmv ይሂዱ ወይም እዚህ ጋር ስካን ያድርጉ።